# NOCOMMENT


ቅጥር 32 ጥቅምት 2005 ዓ.ም
እንግዳችን
በአቶ መለስ ሞት ዙሪያ ከአቶ ዶ/ር አቡሽ ጋር የተደረ



"አቶ ዶ/ር አቡሽ አያሌው እኚህ nebberu"

## በአቶ መለስ ሞት ዙሪያ ከአቶ ዶክተር አቡሽ ጋር የተደረገ ቆይታ

ምንጭ፤ ሎሚ መጽሔት፣ ቁ. 32 ጥቅምት 2005ዓ.ም - (ከገጽ 14 የሚጀምር ቃለ መጠይቅ)

**ሎሚ፦ ባሳለፍነው ዓመት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዜና እረፍት ተሰምቷል፡፡ ስለዚህ የሚሉት አለ?**

**ዶ/ር አቡሽ፦** ምንም የምለው የለኝም፡፡ በውስጤ ማዘን ብቻ፡፡ አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ በሚገባ ገልጾታል፡፡ የጀግኖች ጀግና፣ የአሸናፊዎች አሸናፊ የሆነውን ሰው ነው ያጣነው፡፡ መለስ ብዙ ነገሮችን አሸንፏል፡፡ ደርግን አሸንፏል፡፡ ድህነትን አሸንፏል፡፡ የአፍሪካ መሪዎችን በአዲስ አበባ ጉዳይ ላይ አሸንፏል፡፡ የሕወሓት መሰንጠቅ ወቅት በአሸናፊነት ወጥቶታል፡፡ ሕዝቡን በፍቅር አሸንፏል፡፡ ምዕራባውያንን በዲፕሎማሲ አሸንፏል፡፡ ሌላም ሌላም ! አሁንም ድረስ በጣም፤ እጅግ በጣም ተሰምቶኛል፡፡ ስለአሱ ትኩረት አድርጌ ካሰብኩ እምባየ ይወርዳል፡፡

**ሎሚ፦ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን በአጭር ቃል ግለጹዋቸው ብንልዎት እንዴት ይገልጹዋቸዋል?**

**ዶ/ር አቡሽ፦** ስለመለስ ለመናገር በቅድሚያ ማንነትን ይጠይቃል፡፡ ራስን ማወቅ ይጠይቃል፡፡ ፋይዳ ያለውን ለሕዝብ የሚጠቅም ነገር ሠርቶ ማሳየትን ይጠይቃል፡፡ መናገር ስለቻልን መጻፍ ስለቻልን ወይንም ደግሞ መዝፈንም ስለቻልን ሊሆን ይችላል ፡፡ ስመለስ መናገር አንችልም ብዬ አምናለሁ፡፡ መለስ ጥልቅ ሰው ነው፡፡ ጥልቅ ባህሪ ያለው ሰው ነው፡፡ ተዓምር የሆኑ ውጤቶችን በተጨባጭ ያሳዩ ሰው ነው፡፡ ስለመለስ ለመናገር ከመለስ መስተካከል ወይም ከርሱ የተሸለ ውጤት አምጥቶ በተግባር ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ምናልባት ከርሱ የሚስተካከሉ የልዕለ ኃያል አገር መሪዎች ናቸው፤ መተቸትም የሚችሉት እነሱ ናቸው፡፡ መለስ ደግሞ የነሱ ጓደኛ ነው፡፡ እነሱ ያከበሩት ሰው ነው፡፡ በባህሪው፣ በዕውቀቱ፣ በችሎታው፣ በጥበቡ፣ በተግባሩ ጭምር፡፡ እኔም ስለመለስ ለመግለጽ ገና ብዙ ይቀረኛል፡፡

**ሎሚ፦ በአንተ አስተያየት ወይም የሚመስልህን ያህል...**

**ዶ/ር አቡሽ፦** ካስገደድከኝ ልሞክር፡፡ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ውስጤ የሚነግረኝን ነው የምገልጽልህ፡፡ የዓለም ዝግመተ ለውጥ የት ላይ እንደሚያጠነጥን የተረዳ፣ ያም ደግሞ የኢኮኖሚ ብቃት መሆኑን ቀድሞ የገባው፡፡ በኢኮኖሚያዊ ግብ ላይ ያነጣጠረ ውጤት ለማምጣት የሚያስፈልገው አፈጻጸም ምስጢር የት ላይ እንደሚያጠነጥን የተረዳና የሆነው፤ ያም ደግሞ ባህሪ መሆኑንና በተግባርም ያንጸባረቀው ፡፡ የዓለም የጨዋታ ሕግ እንዴት እንደሚሰራ የተረዳና የተጫወተው፤ ይህም ደግሞ ጌም ቲዎሪ መሆኑን፡፡ መሪነት ምን ማለት

እንደሆነ ተምሳሌት በመሆን ያንጸባረቀው፡፡ የሕይወት ተልእኮ ምን እንደሆነ የገባውና ያሳየው፤ ያም ደግሞ ለሕዝብና ለመጪው ትውልድ መኖር መሆኑን፡፡ የሰው ልጅ በየጊዜው የሚያድግ ፍጡር መሆኑን ያሳየን፤ ያም ደግሞ በመማርና በማንበብ ውስጥ ራሱን ያበቃ መሆኑን፡፡ የከፍተኛ መረጋጋትና በትንሽ በትልቁ የማይፈነጥዝና የማይረበሽ፤ የወደፊት እንጂ የዛሬው ስሜት የማያሸንፈው ሰው ይመስለኛል፡፡ ይህ በእኔ አቅም የተገለጸ ነው፡፡ ብዙ ምርምርና ጥናት ግን ያስፈልገዋል፡፡ ቀጣዩ ትውልድም የዚህ ባህሪ ተጋሪ መሆን መቻል አለበትና፡፡ ለእኔ መለስ በ17ኛው መ/ክ/ዘ ብቅ ካለው ጀግናው ናፖሊዮን ቦናፓርቴ ጋር ባነጻጽረው እችላለሁ፡፡ ነገር ግን መለስ ከናፖሊዮንም በላይ ነው፡፡

***ሎሚ፡- የእርሳቸውን ሳይኮሎጂ ወደርስዎ ሕይወት አምጥተው ሞክረውት ያውቃሉ?***

***ዶ/ር አቡሽ፡-*** በነገራችን ላይ በቀላሉ ኮፒ ልናደርጋቸው የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ፐርሰናሊቲ (ስብዕና) በብዛት ኮፒ አይደረግም፤....

***ሎሚ፡- ጠ/ሚኒስትሩን ለስኬት ያበቃቸው ነገር ምንድነው ይላሉ?***

***ዶ/ር አቡሽ፡-*** ቁርጠኛ ዓላማው ይመስለኛል፡፡ ቁርጠኛ አቋሙ ይመስለኛል፡፡ ቁርጠኛ ራዕዩ ይመስለኛል፡፡ ሁላችንም በአንድ ወቅት እናልፋለን፡፡ የመለስ ቁርጠኛ አስተላለፍ ግን በትውልድ ውስጥ የመኖር ዓላማ ነው፡፡ በትውልድ ውስጥ ለመኖር የቻሉ ሰዎች በዓለም ላይ ጥቂት ናቸው፡፡ መለስ አንዱ ነው፡፡ መለስ ለቁርጠኛ ዓላማው ባህሪውን አስገዝቷል፡፡ አንዳንዴ ዓላማችንና ባህሪያችን ካልተጣጣመ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሌላው የሚመስለኝ የሌሎችን ስኬታማነት አጥብቆ የሚፈልግ መሆኑ ነው፡፡ አየህ፤ ለሌላው ስኬታማነት በሥራህ ቁጥር ተጠቃሚው አንተው ራስህ ነህ፡፡ ለምሳሌ የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ ለመሆን የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃሚነት ወሳኝ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የላቀ ተጠቃሚነት ለመላው ዓለም የሰላምና የልማት ተጠቃሚነት የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ ተጠቃሚነት ወሳኝ ነው፡፡ ለምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ የላቀ ተጠቃሚነት የመላው አፍሪካ ተጠቃሚነት ያስፈልጋል፡፡ በአፍሪካ የላቀ ተጠቃሚነት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ይህን የመለስ መንገድ የሚከተል ይመስለኛል፡፡ ሌላው መለስ ነገሮችን እንደቼዝ መጫወት የሚችል ይመስለኛል፡፡ ይህ በጣም ከባድ ጨዋታ ነበር፡፡ ከባድ አስተሳሰብም ይጠይቃል፡፡ በዚህ ችሎታውም ሌሎች በቀላሉ አያታልሉትም፡፡ ሌሎችን ግን በልጦ መሄድ ይችላል፡፡ ይህ እንደኔ አመለካከት ነው፡፡ በዕውቀት ላይ ...

እያለ... እያለ... እያለ ... የዶክተር ማሙሽ ነው አቡሽ ቃለ መጠይቅ በሎሚ መጽሔት ላይ ይቀጥላል፡፡ ሁሉንም ለማንበብ የፈለገ ሰው ከፍ ሲል በተቀመጠው አድራሻ መሠረት መጽሔቱን አፈላልጎ ማግኘትና መኮምኮም ይችል፡፡

NOCOMMENT የምትለዋ አባባል በ‹euronews› ቲቪ ላይ የማያትና አንድን ሰው ሠራሽም ይሁን የተፈጥሮ ክስተት እንዳለ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ - ለመገረሚያ ወይም ለመዝናኛ ያህል - የሚያስቀምጡባት ግሩም አቅርቦት ናት፡፡ እኔም እዚህ የተጠቀምኩባት የ‹ደራሲ›፣ የነጋዴና የዶክተር ... አቡሽ አያሌውን በይዘትም በቋንቋም ግራ ተጋብቶ ግራ የሚያጋባ ቃለ መጠይቅ እንዳለ ለማሳየት ነው፡፡ በመጨረሻ ግን አላስቻለኝምና ሌላ አጋጣሚን ከምጠብቅ እዚችው ጥቂት ማለትን ወደድኩ፡፡ ዶክተር አቡሽን ብዙ ሰው ያውቀዋል ብዬ እገምታለሁ - በዚህ የጣዖት አምላኪነቱ የተግማማ ስብዕናው ሳይሆን በሌላ መልክ፡፡ ይህ ጎልማሳ ‹ዶክተር› (ለተወሰነ ጊዜ በራሴው ሥልጣን ዱክትርናውን ልቀማውና) ‹ሜዲካል› በሚሰኝ የጋዜጣና መጽሔት ኅትመት ከብዙዎች ጋር ይተዋወቃል፡፡ ይህ ኅትመቱ ፖለቲካን አይነካም፡፡ ዋና ትኩረቱ የማኅበረሰቡን ጤና ነክ ዕውቀት ማጎልበትና የወሲብ ግንዛቤውን ማዳበር ላይ ነው - የሚያሳክከኝ ሌላ ቦታ የሚያክልኝ ሌላ የተለዬ ቦታ፡፡ አንድ አቤ ከቤ ከአርሲ የሚሉት ሥራፈት ሰውዬም አለ - ኤፍኤሞችንና አርቲስቶችን በሙሉ የተቆጣጠረና የሚያመልኩት - አሃ፣ ይሄ ነገር ምቀኝነት ያስመስልብኝ ይሆን እንዴ? ቆይማ ብቻ፣ እርሱንም አንድ ቀን መሞለጬ አይቀርም - አንድ ወቅት በዚያው እንደግል ንብረቱ በሚቆጣጠረው ኤፍኤሙ ሲዘላብድ ‹ከፖለቲካ ጽሑፎች በቀር ሁሉንም ጋዜጣና መጽሔት አነባለሁ› አላለ መሰላችሁ! ያኔ ጥርሴ ውስጥ ገባ፤ ይሄ ቅሌታም የወያኔ አሽቃባጭ፤ ልክ ልኩን ባልነገረው እኔ ጦቢያው አይደለሁም፡፡ ወደ አቡሽ አሁን...

## NOCOMMENT

የዶክተሩን ብዙዎቹን ሀሳቦች ለመረዳት ወደ አማርኛ የሚመልስልኝ ሰው ባፈላልግ አጣሁና ሳይገባኝ ቀረ፡፡ እኚህ ሰው ደራሲ መሆናቸው ሲነገረኝ ደግሞ የሚጽፉትን ማን ሊረዳው እንደሚችል እያሰብኩ መጨነቅ አበዛሁ፡፡ እንዲህ የምለው እውነቴን ነው፡፡ በዚህ ቃለ መጠይቅ በተናገረው የግሉ አቋም ምክንያት ተቀይሜው ያን ልበቀለው እንዳልሆነ በግልጽ መናገር እፈልጋለሁ - አንዴ ‹አንተ›፣ አንዴ ‹አንቱ› የምለው የአፍ ልማድ ሆኖብኝ ነውና አትታዘቡኝ(ዱሮ በወጣትነት ዘመኔ ሴት አማቴን በስህተት ‹ምን ያሉ ናት!› ብዬ ሰውን ማሳቄንና ማሳቀቄን አስታውሳለሁ፤ ጅል ልማድ መጥፎ ነው፡፡)፡፡ ስለመለስ የመሰከረውን እሱና ወያኔ ሼሪኮቹ ብቻ የሚያውቁትን ‹ታላቅ ስብዕ›ና ጊዜው ሲደርስ በአደባባይ ወጥተው በአዲስ መልክ ይመሰክሩታል፡፡

እኔ አሁን የምመክረው ግን ቤተ ጣዖት ቢጤ በቤቱ ውስጥ አዘጋጅቶ ሲተኛና ሲነሳ ለመለስ የሙት መንፈስ እየሰገደ አምልኮቱን እንዲገልጽ ነው፡፡  ይህን ሲያደርግ ደግሞ ዝክር ምስክር ይሆነው ዘንድ የጸሎት ቤቱን በክሎዝ ሰርኪዩት የቪዲዮ ካሜራ የዘወትር ጸሎቱን እየቀረጸ ለሕወሓት የአሻንጉሊቶች ፓርላማ እንዲያስተላልፍ እጠቁመዋለሁ፡፡ በሞተም ይሁን በቁም ባለሰው ማምለክ ደግሞ በእሳቸው በ‹ዶክተሩ› አልተጀመረምና ሊኮራበት ይገባል፡፡ መቅለል የተጀመረው ዛሬ ሳይሆን ከዘፍጥረት አንስቶ ነው፡፡ ትንሽ ዕውቀት ለአደጋ እንደሚዳርግም የተረጋገጠው ዛሬ አይደለም፤ የሞኝ ፍቅር ሆድ እንደሚገትርም ጭምር፡፡ ፍቅር ዕውር መሆኑ ትክክል ነው፡፡ ይህን ጭራቅ ሰው እንዲህን ያህል ለመካብ - ከማያውቁት ናፖሊዮንም በላይ ለማሰቀመጥ - ዶክትሬት ብቻ የሚበቃ አይመስለኝም፡፡ እናም ፕሮፌሰር አቡሽ ጠሙት መንፈስ  ጫማ ሥር ወድቀው እንዲያ በፍቅርና በአምልኮት ሲቃ ሲያቃስቱ አሳዘነኝ፡፡ ያሳፍራል ጎበዝ፡፡ ከመናገር - አይ ቆይማ - ማሰብ በፊት ስለማሰብና ስለምን ማሰብ እንደሚገባ በጥሞና ማሰብ ይገባል፡፡ የሀገርን ምስል - የሕዝብን ንቃተ ኅሊና በሚያጠይም መልክ እንዲህ የመጣልልን እንደንፍጥ የምንዘረፍጥ ከሆነ አዲዮስ ትምህርት! መማር ለመቼ ነው፡፡ ዶክተርዬ ... አቤ ቶኪቻው እባክህን በዚህ ላይ አንዲት ነገር ሥራባት፡፡ ይህችን መልእክትም ለቶኪቻው ስጡልኝ፡፡

እነማራዶና፣ ሂትለር፣ ሙሶሊኒ፣ ኢድአሚን፣ቢስማርክ፣ ቦካሳ፣ ስታሊን፣ ኪም ኢልሱንግ፣ የኛውም መንግሥቱ... ብዙ አምላኪዎች ነበሯቸው፡፡ በነሱ ሲመጡባቸው ደማቸው እንደሽሮ የሚንተከተክና ጦር የሚመዙ፡፡ አቡሽዬም በሚያሳዝን ሁኔታ የነሀሂትለር ጣዖት አምላኪ ሆኖ ተገኙልን፡፡ የገዛጉትን መጽሔት ቀየቶም ቢሆን የማንበብ መጠነኛ ልምድ ስላለችኝ ዛሬ ሳገላብጣት እኮ ነው ጉድ የሆንኩት፡፡ ምን አለ ቢቀርብኝ ኖሮ፡፡ በዚህ ዓይነት ከስንቱ ጋር ተጣልቼስ እዘልቀዋለሁ፡፡ ብዙ ሰው ለካንስ ተግማምቷልና! ብሎ ብሎ መለስን እንዲህ የሚኳሽ ‹ኢትዮጵያዊ› ይገኝ? አይ ዕድሜ ዘልዛላው! ስንቱን ያሳየና/ኛ/ል/? (‹ኧረ ገና ትዘባርቃለች!› አይደል ያለው - ያ መልቲ የንስሃ አባት ካህን - ባለትዳሯ የንስሃ ልጁ እሞት አፋፍ ላይ ሆና ሽማግሌዎች ፊት ስትናዘዝ ‹አምስተኛው ልጄ የሳቸው የመምሩ ነው› ባለች ጊዜ? አዎ፣ ብሏል አሉ፡፡ በምስክር ፊት ስታዋርደው ምን ይበል ዱሮስ? እሷስ አንዱን ይዛዋለች፡፡ እሱ እኮ ለጊዜውም ቢሆን ቀሪ ነው - እናም በተከበረበት ደብርና በተኮፈሰበት ሰበካ ሊዋረድ ነው - እንደአቡሽዬ፡፡

ባለመጽሔቶቹም ‹አቶ ዶክተር› ማለታቸውን ቢያጤኑትና በአርትዖት ቢያስተካክሉት ደግ ነበር - ‹አቶ›ና ‹ዶክተር› አብረው አይሄዱምና - ወታደራዊማዕረጎች፣ ባህላዊ ሹመቶች፣ የዶክተርና ፕሮፌሰር ማዕረጋት ‹አቶ›ን እንደሚፍቁ መረዳት ተገቢ ነው - ውድ ‹ሎሚ›ዎች፡፡ ለነገሩ አንዳንድ የአፍ ወለምታ ልባዊ እውነታን ይገልጻልና ይህ ስህተታቸውእምብዝም ለክፉ አይሰጥም፡፡ ለማንኛውም አቡሽዬን ጌታ ይታደገው፡፡ አምላኩ መለስ ዜናዊም ይለመነው፡፡ ከዚህ ሌላ ምን ይባላል?

(የዚችን ደንቆሮ አዜብ ለፍዳዳ ንግግር የማልሰማበት ሀገር፣ የዚህን የቡቺዬ ኃይለማርያምን ሎሌያዊ የዕዝ ንግግር የማላዳምጥበት ሀገር የት አገኛለሁ? በአሁኒቷ ቅጽበት በጉለሌ አንድ የአትክልትና ዕፅዋት ሥፍራ የመለስ ሙታመት እየተከበረ ነው፡፡ እዚያ ላይ ነው እነዚህ የወያኔ ውሾች ከውጭ ከጋበዟቸው መሰል አምባገነን እንግዶች መካከል ከኢትዮጵያ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ በእጅጉ የሚቃረን ዲስኩር እያደረጉ ያሉት፡፡ እነዚህ ናቸው እንግዲህ መሪዎቻችን፡፡ ‹አላህ ሲቆጣ ሽመል አይቆርጥም፤ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም፡፡›

ጦቢያን ገረመው ነኝ   ከአዲስ አበባ